# ጀግና አይሰደድም!!

ተሰደድ ይሉታል ኧረ እንዴት! ኧረ እንዴት!
ለኢትዮጵያ አገሩ ጥሎ ሳይወድቅላት፡
ጀበርናውን ታጥቆ ይዞ ጠመጃውን፡
ይሸፍታል እንጂ ጀግና አይሰጥም እጁን፡፡
ጀግና አይሰደድም አገሩን አይለቅም፤
ቆሞ ሳይዋደቅ ትንቅንቅ ሳይገጥም፡፡
የቆመባት መሬት ሓብቱናት እርስቱ
በደም የወረሳት ካያቱ ካባቱ፡፡

የኢትዮጵያን ቅርሳቅርስ ሃብት እየዘረፉ
ባገር ስም ለምነው ለግል የገፈፉ፤
አገር አስገንጥለው መሬት እየሸጡ
ባሕር በሯን ዘግተው ወደብ እያሳጡ፡
ታዛቢም እንዳንሆን እኛን ካገር ውጡ!!!
ተዘርዝሮ አያልቅም መቼ ይኸ ብቻ
አዳብሽን እያሉ ወይም ጉዲፈቻ’፤
ሕጻናት መቸርቸር ይዘዋል ዘመቻ፡፡

የወያኔ ነገር “ከገሙ አይቀር ብሽቅጥ”
ወገንን ለዶላር ለኢሮ መለወጥ፣
ጭቃ ማለት፤ ይሕ ነው እንክርዳድ አተላ
ወገኑን እንደከብት ሸጦ የሚበላ፡፡

ሲወድቁ ያነሳን ሙትን የቀበረ፤
አብሮ የታገን ድልን ያበሰረ፡
ታኝን የጦር ጓድ ከጀርባው መውጋት፤
ጭቃነት ይኸ ነው እንክርዳድነት!!
አወይ አደፋፈር ልክን አለማወቅ!
ጥጋብ አልችል ብሎ እንዲሕ መንደላቀቅ!
ይናገራል አሉ እብድና ዘመናይ፤
ማን አለብኝ ብሎ ሌላ ከኔ በላይ፤
ጀግናውን ይሉታል “አገርህን ልቀቅ”
ወይ ስፍራ መመቸት ! አወይ አለማወቅ!!!

ግፉ ሲበዛበት ሲበደል ሲከፋ፡
ይሸፍታል እንጂ መች ካገር ሊጠፋ!!!
ባንዳ ብቻ አይደልም ኢትዮጵያ ያፈራች፤
ወያኔና ሖዳም ጥንብ የተሸከመች፡
ደምን በደም መላሽ ጀግኖችም ወልዳለች፡፡

የጎደለው ጊዜ ቀኑ የሞላለት፡
ወያኔን አያርገኝ!ባንዳውን አያርገኝ!
ሖዳሙን አያርገኝ! እግዚአብሔር ለት!!!!

ይፍሩ ኃይሉ፤

Yhailu05@yahoo.com